# ከደምቢድሎ የታገቱት ወጣት ሴቶች ጉዳይ ዘርፈ ብዙ
# ገጽታና የማንቂያ ደወል

አክሊሉ ወንድአፈረው

ethioandenet@bell.net

ጥር 23,2012 (Febryary 1, 2020)

*"እጅግ ተደናግጬ ራሴን መጠየቅ ጅመርኩ፣ በውነት ይህ ነገር በኔላይ ነው እየሆን ያለው? እዚህ ጫካ ውስጥ ምን እያደረግኩ ነው?እያልኩ ራሴ መጠይቅ ጅምርኩ። ድንገት ከፍተኛ ቅዝቃዜ ተሰማኝና ፣ ድንብርብር ባለ መንፈስ ፣ ይህን አላምንም በፍጹም ሊሆን አይችልም፣ ፈጣሪ ሆይ ይህ መቼም በኔላይ አይሆንም እያልኩ ማጉረምረም ጀመርኩ" አንድ ታጋች ስለደረሰበት ከተናገረው የተወሰደ*

*በሀገራችን ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የህግ የበላይነት ተጥሶ የህዝባችንም የህይወት ዋስትና እጅግ ተናግቶ ይገኛል። ዜጎች ከመኖሪያቸው በባለጉልበቶች ይፈናቀላሉ፣ ባንኮች በጠራራ ጸሀይ ያላንዳች ከልካይ ይዘረፋሉ፣ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ውስጥ በሌሎች ተማሪዎች ከፎቅ ተወርውረው ይገደላሉ፤ ዜጎች የዚህ ድርጅት ደጋፊ ነህ ተብለው ተዘቅዝቀው ተስቅለው በእሳት ይቃጠላሉ፣ ቤተ ክርስቲያኖች ያላንዳች ተው ባይ ይጋያሉ፣ አይነኬ የነበሩ ቀሳውስትን "አባሯቸው" እየተባለ በአደባባይ ይቀሰቀሳል፣ መስጊዶም እንዲጋዩ ይደረጋል፣ ይህን አሳፋሪ ተግባር የፈጸሙትም ጀብዱ እንደሠራ ሰው ሲጨፍሩና ሲፎክሩ ይታያል።*

*አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች የፈልጉት ነገር ካልተደረገ መንግሥትን ያስፈራራሉ፣ አስገድደውም የሚፈለጉትን ለማስፈጸም ይንቀሳቀሳሉ፡ የመንግሥትን አቅድ በጉልበት ያስቆማሉ፣ አንዳንድ ቦታ የአካባቢ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በሚዲያ በኩል ትዕዛዝ ሲሰጡ ይደመጣል፣ በየቦታውም ባለሥልጣኖችን ከሥራ አባርረው የፈልጉትን ይሾማሉ።*

*ይህ ሁሉ ሲሆን መንግሥት በተለይም በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎችና ወንጀል ፈጻሚ ፖለቲከኞች ላይ ድምጹን አጥፍቶ እንዳልሰማና እንዳላየ ሲሆን ይታያል፣ ወይም ድምጹን በለሆሳስ ከማስማት የዘለለ ጉዳይ ሲሠራ አይታይም፣ ወይም ያከናወነው ተግባር ለህዝብ በበቂ አይገልጽም።*

*ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ ብዙዎችን በዚች ሀገር ውስጥ መንግሥት አለወይ?፣ መንግሥት ካለስ ስንት መንግሥት? ወደሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ እንዲሄዱ አስገድዷል።*

*ከላይ የተጠቀሰውን የሀገራችን ሁኔታ በግንዛቤ ውስጥ አስግብቶ ለሚመለከት ነፃ አእምሮ፣ ታግተው እስካሁን (ከ 50 ቀን በላይ) መዳረሻቸው ያልታወቀው የደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ጉዳይ እጅግ አስጨናቂ፣ አሳፋሪና የሚረብሽም ነው። ይህ ሁኔታ ስለ ሀገራችን ሁኔታ ምን ያሳያል? የሚያስከትለው አደጋስ ምንድን ነው? የሚለውን ከተለያየ አቅጣጫ መመርመርና ተገቢ መፍትሄ መሻት እጅግ አጣዳፊ ተግባር ነው። ይህ አጭር ጽሁፍም በዚህ አኳያ ለሚደርገው ውይይት መንደርደሪያ ሀሳቦችን ያቀርባል።*

*እገታ እንደ ፖለቲካ ማሣሪያ*

ቀደም ባሉት ዓመታት ውስጥ የፖለቲካ ብሶትን ለማስማት፣ ዓላማን ለማሳወቅና የሌሎችን ትኩረት ለመሳብ...ወዘተ ብዙ የፖለቲካ ኃይሎች አገታን እንደ አንድ ማሣሪያ ሲጠቀሙበት ኖረዋል። ይህ በአሜሪካም፣ በካናዳም፣ በአውሮፓም፣ በኤሽያና ደቡብ አሜሪካ እንዲሁም በአፍሪካችን የኛን ሀገር ጨምሮ የተከናወነ ተግባር ነበር።

እገታው አንዳንድ ጊዜ አይሮፕላንና ትሳፋሪዎችን መጥለፍ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አጋጣሚን በመጠቀም ትኩረት ሳቢ የሆኑ ዜጎችን ማፈንን ያካተተ ነበር። ከነዚህም ውስጥ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ 1968 የፓለስታይኑ ነፃ አውጪ ግንባር (Popular Front for the Liberation of Palestine ) የእስራኤልን አየር መንገድ ኢል አል (El Al ) እና ተሳፋሪዎቹ ላይ ያደረገው ጠለፋ፣ በ 1972 ጥቁር መስከረም (ብላክ ሴፕተምበር) የተሰኘው የፓለስታይኑ ድርጅት በጀርመን ሚዩኒክ ኦሎምፒክ ዝግጅት ላይ የእስራኤል ስፖርተኞችን በማፈን ያደረሰው ግድያ፣ በሰሜን አየርላንድ፣ በአይ አር ኤ (IRA)፣ የጀርመኑ ሬድ ብርጌድ፣ በባስክ ስፔይን...ወዘተ የተካሄዱ ሁሉ አገታን እንደ ፖለቲካ መሣሪያ በመጠቀም ረገድ የሚጠቀሱ ናቸው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ከፖለቲካ ጋር ተዛምደው በተካሄዱ የግለሰብም ሆነ ስፋ ያለ የቡድን ጠለፋዎች ሲታሰቡ የአፍጋኒስታኑ ታሊባን (Taliban,) የኢራቁና ሶርያው ኢስላሚክ እስቴት (ISIL) የዩጋንዳው ሎርድስ ሪዚስታንስ አርሚ ( Lords Resistance Army)፣ የናይጀሪያው ቦኮ ሀራም፣ (Boko Haram) የጎረቤታችን ሶማሊያ አልሸባብና የመሳሰሉት ያካሄዷቸው ሁሉ የሚጠቀሱ ናቸው።

እገታን እንደ ፖለቲካ መሣሪያነት የሚጠቀሙ ከፍሎች አንዱ ግባ የፖለቲካ ድርጅቶች በመንግሥት የታሰሩ የድርጅቶቻቸውን አባላት ወይም ደጋፊዎች በልውውጥ ለማስፈታት፣ በድርጅቱ ላይ በመንግሥት የሚደረግን ጥቃት ለማስቆም፣ ወይም ቀዝቀዝ እንዲል ለማድረግ ታጋቾቹን በመደራደሪያነት ለማቅረብ የሚደርግ ሙከራ አንዱ ነው።

የደምቢደሎ ሴት ተማሪዎችን ጠለፋና እገታ ከላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ ምክንያቶች አንፃር በመመርመር የሁኔታውን ምንነትና የተጋረጠውንም አደጋ ለመገንዘብ ዕድል ይሰጣል።ጠለፋው ተካሄደ የሚባልበትን አካባቢ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሁኔታ ስንመርምር ደግሞ ጠለፋውን ሊያካሂዱ ከሚችሉ ክፍሎች ውስጥ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡

በጃል መሮ የሚምራው አነግ ፡

ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ጠለፋን ለማካሄድ እጅግ ጠንካራ ድርጅትንና ጥልቀት ያለው እስትራትጂያዊ ጥናት ባያስፍልግም፣ በቁጥር ስፋ ያሉ ሰዎችን ጠልፎ ከመንግስት ጥቃት እየተከላከሉ ከ 50 ቀን በላይ ለመቆየት አንጻራዊ ጥንካሬ ያለው ድርጅት ያስፈልጋል። ላልፉት 18 ወራት በጃል መሮ የሚምራው አነግ ውጭ በአካባቢው መሳሪያ ታጥቆ የሚንቀሳቀስ አንጻራዊ ጥንካሬ ያለው ድርጅታዊ ሀይል እንደሌለ የሚታውቅ ነው።ከዚህ በተጨማሪም ፣ ይህ ድርጅት ባለፈው 18 ወራት ውስጥ በተለያዩ የባለስልጣኖች ግድያ፣ ጠለፋና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዋነኛው ተጠርጣሪ ሆኖ ቆይቷል። ከእነዚህን ሁሉ ጋር አያይዘን ስንመለከትም ለጠለፋው በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ መንገድ ሸኔ በዋና ተጠርጣሪነት የሚታይ ይሆናል።

በርግጥም እነዚህ ሴት ወጣቶች የታገቱት በኦ ኤል ኤፍ (OLF ሸኔ ) ከሆን የዚህ ጠለፋ ያሁኑ ግብ ወጣቶች ከመታገታቸው ጥቂት ቀደም ብሎ መንግስት በድርጅቱ ላይ የጀመረውን ወታደራዊ ጥቃት ለማስቆም ያስበ ነው ወደሚለው መደምደሚያ የሚያመላክት ይሆናል።

የሸኔ፣ የፖለቲካ አጀንዳ እጅግ ሰፊና ውስብስብ ሲሆን ዘላቂ መፍትሄ ፍለጋውን በተመለከተም በአባ ገዳዎች፣ በሌሎች ፖለቲከኞችና ተጸእኖ ፈጣሪዎች ትብብር እስካሁን ግጭቱን የሚያስቆም አመርቂ መፍትሄን ማግኘት አልተቻለም። ሸኔ ደግሞ ደጋግሞ በሚያስማው ድምፅ የአለም አቀፉን ህብረተሰብ (ሶስትኛ ወገን) ጣልቃ ገብነት የሚጋብዝ ነው። ይህም በመሆኑ ደርጅቱ ከሚሻው መፍትሄ ውስብስብነት አንጻር ሲታይ እገታው ረጅም ሰላማዊ መፍትሄውም ሩቅ እንደሚሆን ይጠቁማል።

ሌሎች ተጸእኖ ፈጣሪዎች

በዚህ ጠለፋና እገታ ሌሎች ተጠርጣሪ ሊሆኑ የሚችሉ ክፍሎች ራሳቸውን ልል በሆን መልክ በቡድን ያደራጁና በአካባቢው ሁኔታ ላይ የተለያየ ተጸእኖ ፈጣሪ ከሆኑ ግለስቦችና ስብስቦች ጋር ቀጥተኛም ሆነ ተዛዋሪ ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ

አካባቢ በቀል  ሀይሎች ናችው። የነዚህ ሀይሎች ዋና አላማ የፖለቲካ ውጥረትን በመፍጠር የተወሰን የፖለቲካ አጀንዳን ማራመድና የማይፈልጉትንም የመንግስት እርምጃ ማደናቀፍ ሊሆን ይችላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ  በሀገራችን ውስጥ የመንግስትን ወይም የገዥውን ቡድን  የተለያዩ አጀንዳዎች በጉልበትና የተለያዩ ቀወሶችን በመፍጠር ለማስቆም መሞከር (ማስቆም ) እየተለመደ እንደመጣ የሚታወቅ ሀቅ ነው። እገታው በተጠቀሱ ክፍሎች ቀጥተኛም ሆነ ቀጠተኛ ያልሆን ተእዛዝና ተጽእኖ የተፈጸም ከሆነ  የአጋቾቹ ፍላጎት የፖለቲካ አጀንዳን ማስፈጸም ስለሆን ታጋቾቹን  በድርድርና በሰላም ብቻ  ለማስለቀቅ የሚደረገው  ጥረት የተሻለ ውጤት የማስግኘት እድል ቢኖረውም ቀላል እንደማይሆን ግን መገምት ይቻላል።

የአጠቃላይ አለመርጋጋትና ግጭት ተጠቃሚዎች

በሶስተኛ ደረጃ እገታው የአካባቢውንም ሆነ የመላ ሀገሪቱን መረጋጋት የማይሹ ፣ በተለያየ ምክንያትም ግጭት እንዲቀስቅስና እንዲስፋፋ የሚፈልጉ (የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ) ሀይሎች ረጅም እጅ ያለበት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይችላል ። የነዚህ ሀይሎች  እንቅስቃሴ ከመጀመሪያውም በበቂ ማቴርያል ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ሰለሚሆን ታጋዮችን ለማስለቀቅ በገንዘብ ሀይል ለማግባባት የሚችልበት ሁኔታ እጅግ ዝቅተኛ ነው።

ይህ ሁኔታ ከታጋቾች ማንነት አንጻር ሲመረመር  በዋናነት ከአማራ ክልል በመጡ ከገዥው ፓርቲ ጋር ምንም ግንኙንት በሌላቸው ሴት ወጣቶች ላይ ለምን አተኮረ ፣ የጠላፊዎች  የፖለቲካ ችግር  ከመንግስት ባሻገር ከአማራ ህዝብ ጋር ነውን? አላማቸው አካባቢውን አማራ ጠል አድርጎ ማሳየት ነውን ፣ በአማራውና ኦሮምኛ ተናጋሪው ህዝብ መሀል ያለውን ግንኙነት ለማሻከር የተጠመደ ፈንጂ ይሆን ? ከዚህ ሁሉ ተጠቃሚውስ ማን ሊሆን ይችላል? የሚሉት ጥያቄዎች መነሳታችው የግድ ነው።

ጠለፋውም ሆነ እገታው ከተወስን የፖለቲካ አላማ ጋር ተያይዞ የተፈጸመ ሆነም አልሆነም ታጋቾች በመታገታችው ብቻ ከሚደርስባችው ስቃይ ባሻገር ለሌሎች ተጨማሪ አደጋዎችም ተጋላጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በተለያዮ ቦታዎች የተካሄዱ ተመሳሳይ እገታዎች  አመላካች ናቸው።

አገታ አስግድዶ መድፈርና  ሌሎች የስቃይ ተግባሮች (ቶርቸር)

ብዙውን ጊዜ እገታ የሚያካሂዱ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች እንዱና የመጀመሪያ እርምጃቸው ታጋቾችን በኃይለኛ ፍርሃት እንዲዋጡ፣  አጋቾቻቸው  የሚሿቸውን  ሙሉ  በሙሉ  እንዲፈጸሙ  ይህን  ካላደርጉም  በራሳችውም  ሆነ  በሌሎች የሚያውቋችው ሰዎች ላይ የበለጠ አደጋ ይደርሳል ብለው እንዲያምኑ ማድረግ ነው። በሚወስዷችው እርምጃዎች  ታጋቾች ሥነልቦናዊ ጥንካሬያቸው በአጠቃላይ ተሚጦ እንዲጠፋ የማምለጥም ሆነ ሌላ የአምቢታ ተግባርን ለመፍፀም የሚያስችል የፅናት ስሜታችው ሙሉ በሙሉ እንዲሰበር ያደርጋሉ። ይህን የሚያደርጉት በታጋቾቹ ላይ ሙሉ ቁጥጥርን ለማስፈን ነው።

ይህን ተግባራዊ ከሚያድርጉበት መንግዶች ውስጥ፣ አስቃቂ ድብደባና ሌሎች የግፍ ተግባሮች (ቶርቸር) መፈጸም ፤እንቅልፍ በመከልከል የአእምሮ ሁከትና በትክክል ማስብ እንዳይችሉ ማድረግ አልፎ ተርፎም አስግድዶ መድፈር፣ ዋነኛዎቹ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ከናይጀሪያው ቦኮ ሀራም እስከ ዩክሬይን፣ ከቦሊቪያ እስከ ህንድ፣ ኢራቅና ሶርያ የታየው የጠለፋና እገታ ታሪክ በአብዛኛው ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች አስቃቂ ተግባሮችን ያጠቃለለ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በሩዋንዳ፣ ቦዝንያና ሌሎችም ቦታዎች እንደታየው "የጠላትን ሴቶች" ከባለሥልጣናት እስከ ዘበኛ አስግድዶ መድፍር እጅግ የተዘወተረ ተግባር ነው፡፡ ተመሳሳይ መረጃ ለማየት የሚከትሉትን በመጫን ያንብቡ http://www.meredethturshen.com/www/pdf/WorldBankRapechapter.pdf

ከዚህ ለማስብ የሚከብድ ስቃይ በተጨማሪ እጅግ የሚዘገንነው ደግሞ አጋቾች በታጋቾች ላይ ከላይ የተጠቀስውን አሳፋሪ እርምጃ ከወሰዱ በኋላ ታጋቾችን ለመልቀቀ የሚኖራቸው ፍላጎት እጅግ ዝቅተኛ እየሆነ የሚምጣ መሆኑ ነው። ይህ የሚሆነውም ታጋቾች ነፃ ቢሆኑ ስለደረስባቸው ግፍ ይናገራሉ፣ ይህም በወንጀል ተፈላጊነታችንን ከባድ ያደርግዋል፣ በኅብረተሰቡ ውስጥም ድጋፍ ያሳጣናል ብለው አጋቾች ሰለሚያስቡ ሲሆን ከዚህ አዘቅት ለመውጣት የሚከተሉት ጎዳና ብዙውን ጊዜ ታጋቶችን እንዳገቱ መቆየት ወይም ሚስጥራቸውን እንደያዙ በመግደል ወደተጨማሪ አዘቅት መግባት ነው፡፡

በታገቱት እህቶቻችን ላይ ከላይ የተገለጸው አንዱም እንዳይፈጸም ብመኝም፣ ይህ ኢ-ሰብዓዊ ጭካኔ እውን ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ መሆኑን ያለምንም መደባበቅ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው።ይህ እውነታ ታጋቾችን ነጻ የማውጣት ሃላፊነት አጥፍ ድርብ ያደርገዋል።

እገታ የረጅም ጊዜ የአእምሮ ቁስልና ያልተረጋጋ ኅብረተስብንም ይፈጥራል

እገታ በታጋቾች ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ፣ ወዳጅና ዘመድ እንዲሁም ይህ ሁኔታ በሚካሆኄድብት አካባቢ ውስጥ በሚኖሩ ላይ ሁሉ የሚያደርሰው የአእምሮ ጤና መናጋትና በእርስ በርስ ግንኙነት ላይ የሚኖር አሉታዊ ተጽእኖ ወዘተ ከፍተኛ መሆኑን ብዙ ጥናት ያሳያል። ለምሳሌ ከፍተኛ መደበት፣ ከፍተኛ ጭንቀትና የምንፈስ አለመረጋጋትና፣ ከፍተኛ ድንጉጥነትን የመሳሰሉትን የአእምሮ ህመሞች እንደሚያስክትል፣ በቤተስብና በኅብረተስብ ደረጃ ደግሞ ከፍተኛ አለመተማመንንና ጭንቅን እንደሚያስፍን ብዙ ምርምሮች አረጋግጠዋል።

ከላይ የተጠቀስው ቀውስ የአንድ ሰሞንና በእገታው በቀጥታ የተጠቁ ሰዎች ችግር ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ረጅም ዋጋን የሚያስክፍል ሊሆንም ይችላል። ስለዚህ የታገቱት ወጣት ሴቶች ካሁን በኋላ ነፃ ቢሆኑ እንኳን ወዳጅና ዘመድ ትላንት የሚያውቃቸው ሰዎች አይሆኑም። በስቃዩ ምክንያት ህይወታቸው መሠረታዊ በሆነ መንገድ ተለውጧል።

ምን ይደረግ?ן

እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ እገታው በማን እንደተካሄደ፣ የአጋቾቹ ፍላጎትን የጠለፋው ዓላማ ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ግልጽ አይደለም። ይህ ሳይሆን ጊዜው እያለፈ በሄድ ቁጥርም የታጋቾቹ ደህንነት እጅግ አሳሳቢ፣ መኖራችውም አጠራጣሪ እየሆነ ይመጣል።

የተጠለፉትና የታገቱት ወጣት ሴቶች የሚገኙበት ሁኔታም ሆነ በትክክል በማን እንደታግቱ በመንግሥት በኩል እስካሁን የቀረበው መግለጫ እርስ በርስ የተምታታ ተጨባጨነትም ሆነ ግልጽነት የጎደለው ወይም ደግሞ በበቂ ደረጃ ያልተብራራ ነው።

ይህም በመሆኑ በአጋቾቹ ላይ ከሚታይው የቁጣ ሰሜት ያላነስ ወቀሳ በመንግሥት መሪዎች ላይ ተነጣጠሮ ይታያል። ብዙ ሰው መንግሥት ይህን ጉዳይ ለመፍታት ፍላጎትም ችሎታም አለው የሚለው እምነቱ በፍጥነት እየተቦረቦረ ነው።በጃንዋሪ 28,2020 በአማራ ክልል ብዙ ከተሞች የተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ የዚህ አንዱ መገለጫ ነው።

መንግሥት በዚህ ሁኔታ ላይ ወቅታዊ፣ ግልጽና ተአማኒነት ያለው መረጃ ባለመስጥቱም ህዝብ ለተለያዩ መላምቶችና ተባራሪ መረጃዎች ተጋልጧል።

ይህ ሁኔታ መፍትሄ ሳያገኝ እየተጓተተ በሄድ ቁጥር የኅበረተሰቡም ቁጣ እጅግ እያደገና እየከረረ መምጣቱ አይቀርም። ይህ ደግሞ እጅግ በተካረረው የሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ አላስፈላጊ ወደ ሆነ ግጭትና አለመርጋጋት የሚሄድበት ዕድል ሰፊ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ዜናው ዓለምአቀፍ ሽፋን አያገኘ በሄድ መጠን ቱሪዝምን ይገድላል፣ ኢንቪስትመንትን ያሸሻል፣ ዓለምአቀፍ ተጽእኖን ያጠናክራል፣ ኅብረተስብን ያልተረጋጋ ያደርጋል፣ መንግሥትን ክብር ያሳጣል፣ ህግ-አልባነትን ያበረታታል፤ ለጨለምተኞች ሁሉ ሰፊ በር ይከፍታል።

ከዚህ ለመውጣት ቢያንስ የሚከትሉት ተግባራት በአጣዳፊ ሊከናወኑ ይገባል፡

*መንግሥት ግልጽ ተዓማኒና ተጨባጭ ወቅታዊ መርጃ በተከታታይ ለህዝብ ማቅረብ ይኖርበታል*

*መንግሥት በጠላፊዎቹ ላይ ስብአዊ መብትን የማይጥስ የማያዳግም ጠንካራ እርምጃ በመውስድ የታገቱትን ሁሉ ነፃ ማውጣትና ወደ ስላማዊ ኑሯቸው መመለስ ይኖርበታል፡*

*ታጋቶች ነጻ ሲሆኑ ( ወዳጅ ዘምዶቻቸውን ጨምሮ ) የሚገጥማቸው የስነ ልቦና የጤናና ሌሎችም ቀውሶች በመገንዘብ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለመስጠት ዝግጅቱ ከአሁኑ መጀመር ይኖርበታል፡*

*በአጋቾች ላይ የማያመነታ ስብአዊ መብትን የማይጥስ ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ መንግሥት ለታጋቾችም ሆነ ለሌላው ህዝብ ደህንነት ያለውን ሀላፊነት ለመውጣት ዝግጁ እንደሆነ፣ ለህግ የበላይነት እንደቆመና ለዚህ ዓይነት ወንጀል ምንም ትዕግሥት እንደሌለው ማሳየት ይኖርበታል*

*ህግ የማስከብር ተግባር የገጠመው አደጋ አየስፋ ነው፣ መንግሥት ይህን ከቀን ወደ ቀን እየመነመነ የመጣውን በተቋማት ላይ እምነት ማጣትን በአስቸኳይ መልሶ መገንባት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ አደጋው ለራሱ ለመንግሥት ህልውና ብቻ ሳይሆን ለሀገር ተረጋግቶ መቀጠልም ጭምር ነው፡*

ከአማራ ክልል በመጡ ተማሪዎች ላይ የደረሰው ጠለፋ ነገ በማንኛውም ኢትዮጵያዊም ሆነ የውጭ ዜጋ ላይ ሊደርስ እንደሚችል መጠራጠር የለብንም፡ የአሁኑ ጠለፋና እገታ የሚያስገኘው ጠቀሚታ (ሪዋርድ reward ) ከሚያስከትለው ኪሳራና ቅጣት (ፓኒሽምንት punishment) የሚበልጥ እስከሆን ድረስ ይህ ወንጀል ተጠናከሮ እንደሚቀጥል መገመት ይቻላል። ተግባሩን የፈጸሙት ብቻ ሳይሆኑ ይህን የሚመለከቱ ሊሎችም ተመሳሳይ ተግባር ውስጥ እንዲሰማሩ ሊያበረታታ ይችላል። ይህ ታላቅ ተግዳሮትን የሚፈጥር አደገኛ አዝማሚያ ነው፡፡ ለዚህም ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚባለው ሁኔታው ይበልጥ ሳይሰፋፋ ከአሁኑ ከሥር መሠርቱ መፍታት የግድ ይላል።

*ይህን እያደገ የመጣ ታላቅ አደጋ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሃይማኖትና ሌሎችም ተቋሞች፣ እንዲሁም መላው ህዝብ በጋራ ደግመው ደጋግመው ሊያወግዙት ይገባል።*

*ሁኔታዎች ባስቸኳይ ካልተቀየሩ የአካባቢው ፖለቲካዊ አለመርጋጋት አሁን ካስከተለው የባስ አደጋንም ሊደቅን ይችላል። ብዙ ጥፋትንም ይጋብዛል። ስለዚህም ባካባቢው በመሳሪያ ሀይል ተደግፈው የሚንቅሳቀሱ ሀይሎችን ችግሮች በስላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረቱ ያለመታከት መቀጠል ይኖርበታል። ሀገራችን ከአመጽና ከመሳሪያ ፍልሚያ አዙሪት ልትውጣ በየትም ቦታ የሚገኘው ወገናችንም ሰላማዊ አየር ለመተንፈስ እድል ሊያገኝ ይገባል።ይህ የስላም ፍሊጋ ሂደት በአንድ አካባቢ ተወስኖ ሳይቀር ሁሉን አካታችና ሀገር አቀፍ ማድረግ ከዚህም በመነሳት ብሄራዊ መግባባት ላይ መድረስ አሁንም ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር ነው።*

*ማጠቃለያ*

የተከሰተው አሳዛኝ ሁኔታ ለመንግሥት አሁንም ሌላ የማንቂያ ደወል ሊሆነውና እስካሁን በተለያየ ምክንያት ያልወሰዳቸው ህጋዊ እርምጃዎች፤ ያላካሄዳቸውን የአመለካከት ለውጦችን የፖሊሲ ውሳኔዎች…ወዘተ በስፊውና በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲያደርግ ሌላ ማሳሰቢያና ግፊት ሰጠቶታል። ይህን በማድረግም ህገርና ህዝብ ከቀን ወደ ቀን እየገቡበት ከሚገኘው አስከፊ ዝቅጠት ሊታደግ ይገባል።